**የኮረና ወረርሽኝ በታክስ ከፋዩ ላይ ያደረሰውን ጉዳት ለመቀነስ**
**የወጣ የታክስ ዕዳ ምህረት መመሪያ ቁጥር 248/2013**

1. **አውጪው ባለስልጣን**

የገንዘብ ሚኒስቴር በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 በተሰጠው ስልጣን ማስረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ለኢኮኖሚ ማነቃቂያ ተብሎ የተደረገውን ወዝፍ የታክስ ዕዳ ሜቃለያ ወሳኔ ለማስፈፀም ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

**ክፍል አንድ**
**ጠቅላላ ድንጋጌዎች**

2. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የኮረና ወረርሽኝ በታክስ ከፋዩ ላይ ያደረሰውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣ የዕዳ ምህረት መመሪያ ቁጥር 248/2013 "ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. **ትርጉም**

በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ወይም በፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 ትርጉም የተሰጠው ቃል በዚህ መመሪያ ወስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ በታክስ አስተዳደር አዋጁ ወይም በገቢ ግብር አዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ወስጥ ፡-

ሀ/ "ምድብ "ሀ"" ማለት የኢትዮጵያን በጀት ዓመት ተከትለው ዓመታዊ ሂሳባቸውን ለሚዘጉ ታክስ ከፋዮች እስከ 2007 ዓ.ም ፣ የግሪጎሪያን አቆጣጠር ተከትለው ዓመታዊ ሂሳባቸውን ለሚዘጉ ታክስ ከፋዮች እስከ 2014 ያሉትን የግብር ዘመናት የያዘ ምድብ ነው፡፡

ለ/ "ምድብ 'ለ'" ማለት የኢትዮጵያን በጀት ዓመት ተከትለው ዓመታዊ ሂሳባቸውን ለሚዘጉ ታክስ ከፋዮች ከ2008 ዓ.ም እስከ 2011 ዓ.ም፣ የግሪጎሪያን አቆጣጠር ተከትለው ዓመታዊ ሂሳባቸውን ለሚዘጉ ታክስ ከፋዮች ከ2015 እስከ 2018 ያሉትን አራት የግብር ዘመናት የያዘ ምድብ ነው፡፡

ሐ/ "የማግስት ወሳኔ" ማለት በኮረና ወረርሽኝ ምክንያት የኢኮኖሚ ጉዳት የደረሰበትን ታክስ ከፋይ እንዲሁም በሌለው የማህበረሰብ ክፍል ላይ እየደረሰ ያለውን የኑሮ ጫና ለመቀነስ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የተሰጠ ወሳኔ ነው፡፡

መ/ "የታክስ ዕዳ ምህረት" ማለት ማንኛውም በታክስ ሕግ መሠረት የሚጣል ፍሬ ታክስ፣ ወለድና ቅጣት በምህረት ቀሪ እንዲሆን የተሰጠ የማግስት ወሳኔ ነው፡፡

ሠ/ "የክፍያ ጊዜ" ማለት በማግስት ወሳኔ ማስረት ፍሬ ታክስን ለማከፍል የተሰጠ እስከ አንድ ዓመት ድረስ ያለ ጊዜ ነው፡፡

ረ/ "ታክስ" ማለት በምድብ "ሀ" እና በምድብ "ለ" ባሉት ጊዜያት ያለ ፍሬ (ዋና) ታክስ፣ ወለድ ወይም ቅጣት ሲሆን ከእነዚህ ወስጥ አንዱን፣ ሁለቱን ወይም ሶስቱን የያዘ ሊሆን ይችላል፡፡

ሰ/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም የገቢዎች ሚኒስትር ነው፡፡

## 4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ፡-

1/ በገቢ ግብር አዋጅ፣ በማዕድን ስራ ገቢ ግብር አዋጅ፣ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ፣ በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ፣ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ፣ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ድንጋጌዎች ማስረት ተወስኖ ለክፈል የሚገባን እስከ 2011 ዓ.ም (እ.ኤ.አ.እስከ 2018) ባሉት የግብር ዘመናት ላይ ያለን የታክስ ዕዳ የሚመለከት ሲሆን፤ የታክስ ባለስልጣኑ በወኪልና በሚሰበስበው ታክስ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

2/ በዚህ መመሪያ የተመለከተው የታክስ ዕዳ ምህረት እና ወለድና መቀጫ የማንሳት ወሳኔ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉት በአገልግሎት፣ በማምረት፣ በወጪ ንግድ፣ በፋይናንስና ኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሰማሩ ታክስ ከፋዮች ናቸው፡፡

## ክፍል ሁለት

## <u>በምድብ "ሀ" የሚገኙ የግብር ዘመናት የወዝፍ ዕዳ ቀሪ አደራረግ</u>

## 5. <u>የወዝፍ የታክስ ዕዳ ቀሪ አደራረግ ሥርዓት</u>

1/ በምድብ "ሀ" በተጠቀሰው ግብር ዘመን በታክስ ወሳኔ ማስታወቂያ ላይ የተገለጸው ቀሪ ወዝፍ የታክስ ዕዳ ማጠን በምህረት ቀሪ ሆኗል፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 1 የተገለጸው ቢኖርም፣

ሀ) ከሚኒስቴሩ መ/ቤት ውጭ ላሉ አካላት የታክስ አቤቱታ ለማቅረብ ክፍያ የከፈለ እና/ወይም፣

ለ) በታክስ ወሳኔ ማስታወቂያ ላይ የሚታየውን የታክስ ዕዳ ማጠን ይህ ወሳኔ ከማስጠቱ በፊት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የከፈለ ታክስ ከፋይ፣ ሌላ ተጨማሪ ክፍያ ሳያስፈልግ የከፈለው በቂ ሆኖ ቀሪው የታክስ ዕዳ በምህረት ቀሪ ይሆናል፡

3/ ከምድብ "ሀ" ወስጥ በታክስ ወሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት፣ በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም በየደረጃው ባለ መደበኛ ፍርድ ቤት የታክስ ክርክር ያለው ታክስ ከፋይ በክርክሩ ለመቀጠል የሚፈልግ ስለመሆኑ ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ወስጥ ለታክስ ባለስልጣኑ ካላሳወቀ ይህን ወሳኔ እንደተቀበለው በመውሰድ እንደ ሁኔታው የዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር (1) ወይም (2) ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር (3) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ታክስ ከፋዩ የታክስ ወሳኔ ማስታወቂያ የደረሰወና ለታክስ ወሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት የታክስ ወሳኔ ቅሬታ አቅርቦ ቅሬታው በመታየት ላይ ያለ ከሆነ ክርክሩ የሚቋረጥ ሲሆን የጉዳዩን መቋረጥ ጽህፈት ቤቱ ለታክስ ከፋዩ በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡

5/ በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም በየደረጃው ባለ መደበኛ ፍርድ ቤት በተሰጠ ወሳኔ ላይ የታክስ ባለሥልጣኑ ወሳኔወን በመቃወም አቤቱታ ያቀረበ ከሆነ የታክስ ባለስልጣኑ ያቀረበወን የታክስ ክርክር የተወ ስለመሆኑ ጉዳዩ ለተያዘበት አካል እና ለታክስ ከፋዩ በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (5) የተመለከተው ቢኖርም ታክስ ከፋዩ ለፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ በፍርድ ወሳኔ መሠረት የግብሩ ማጠን የተሻሻለ ከሆነና ይህ የተሻሻለው ማጠን ግብር ከፋዩ ካስያዘው ገንዘብ ያነሰ ከሆነ ልዩነቱ ለታክስ ከፋዩ ይመለሳል፡፡

7/ በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም በየደረጃው ባለ መደበኛ ፍርድ ቤት በተወሰነው ወሳኔ ላይ በታክስ ከፋዩ ወይም በታክስ ባለስልጣኑ ቅሬታ ቀርቦ በመታየት ላይ ባሉ ጉዳዮች ለየግብር ዘመኑ ለሚጨረሻ ጊዜ በቅሬታው ላይ በተሰጠው ወሳኔ መሠረት የተሰጠው የታክስ ወሳኔ ማስታወቂያ የወዝፍ ዕዳ ማጠን ተደርጎ በወሳኔው መሠረት የሚፈለገው የታክስ ዕዳ ቀሪ ይደረጋል፡፡

8/ ታክስ ከፋዩ በታክስ አስተዳደር ሕግ መሰረት የታክስ ቅሬታወን የሚያቀርብ መሆኑን ካልገለጸ በስተቀር መንግስት በሰጠው ወሳኔ መሰረት በምድብ "ሀ" ወስጥ ያለ የታክስ ዕዳ ቀሪ ስለመደረጉ ለታክስ ከፋዩ የጽሁፍ ማረጋገጫ በታክስ ባለስልጣኑ ይሰጣል፡፡

9/ መንግስት በሰጠው ወሳኔ መሠረት ለማስተናገድ የሚይፈልግና በታክስ አስተዳደር ሕግ መሰረት ቅሬታ የማቅረብ ሂደቱን መከተል የሚፈልግ ታክስ ከፋይ ቅሬታው ቀርቦ በተሰጠው ወሳኔ መሠረት የተሻሻለ ታክስ ወሳኔ ማስታወቂያ በታክስ ባለስልጣኑ የሚሰጠው ሲሆን ቀጣይ ሂደቱም የታክስ ሕጉን ተከትሎ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

10/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር (3) እና (6) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በታክስ ወሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት፣ በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም በየደረጃው ባለ መደበኛ ፍርድ ቤት ተወስኖ በወሳኔው መሰረት እንዲስተካከል የታክስ ወሳኔወን ለወሰነው ለታክስ ባለስልጣኑ የስራ ክፍል የተመለሰ ከሆነ ታክስ ከፋዩ ወደ ቀጣይ የቅሬታ ደረጃ ይግባኝ የሚጠይቅ ካልሆነ በስተቀር ወሳኔ ማስተካከሉ ይቋረጣል፡፡

11/ በምድብ "ሀ" ወስጥ በሚገኝ የግብር ዘመን የታክስ ዕዳ ኖሮበት በክፍያ ስምምነት ላይ ያለ ታክስ ከፋይ የመንግስት ውሣኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ሳይከፈል በቀሪነት የሚታየው የታክስ ዕዳ በታክስ ከፋዩ ማመልከቻ ማቅረብ ሳያስፈልግ ቀሪ ይደረጋል፡፡

12/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (6) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በምድብ "ሀ" ወስጥ ያለን የግብር ዘመን የሚመለከት ሆኖ በተለያየ ምክንያት ማለትም በታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት፣ ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም ለፍ/ቤት ይግባኝ ለማቅረብ የተከፈለ ክፍያ፣ ቅድመ ግብር ክፍያ፣ በትርፍ የተከፈለ ታክስ ወይም ሌላ ገቢ ግብርን የተመለከተ ክፍያ ተመላሽ አይደረግም፤ ለሌላ የግብር ዘመን ዕዳም ማካካሻ አይወልም፡፡

13/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ወሳኔ መሠረት ምህረት ከተደረገው የታክስ ዕዳ ማጠን በላይ ያለ የምድብ "ሀ" የታክስ ዕዳ ለገንዘብ ሚኒስቴር እየቀረበ በምህረት ቀሪ ይደረጋል፡

## 6. <u>በዕዳ ምክንያት የተያዘ ሀብትና ንብረት</u>

1/ በምድብ "ሀ" ወስጥ በሚገኝ የግብር ዘመን ታክስ ተወስኖ መክፈል ባለበት ጊዜ ባለመክፈሉ ምክንያት ለታክስ ዕዳው ማካካሻ ይሆን ዘንድ የተያዘ የማንቀሳቀስ ወይም የሚንቀሳቀስ ሀብት ለባለሀብቱ ተመላሽ የሚደረገው የግብር ዕዳው የሚፈለግበት ድርጅት በኢኮኖሚው ወስጥ በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ሲሆን ብቻ ነው፡፡

2/ በኢኮኖሚው ወስጥ በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ድርጅት መሆኑን ለሚረጋገጥ የሚቀርበው ማስረጃ በሚኒስቴሩ ይወሰናል፡፡

3/ በኢኮኖሚው ወስጥ በመንቀሳቀስ ላይ ላለ ድርጅት የተያዘው ንብረት ሊመለስ የሚችለው ከ2008 ጀምሮ የሚፈለግ ዕዳ የሌለበት ሲሆን ብቻ ነው፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የተያዘ ንብረት ተመላሽ የሚደረግለት ታክስ ከፋይ ንብረቱን እንዲረከብ በማስታወቂያ ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ወስጥ ንብረቱን ካልተረከበ ንብረቱ ለመንግስት ገቢ ይሆናል፡፡

5/ በምድብ "ሀ" ወስጥ ያለ በመንቀሳቀስ ላይ ድርጅት ከሌሎች ባለገንዘቦች በሚፈለግ ዕዳ ምክንያት ንብረቱ በተጨማሪነት በፍርድ ቤት የታገደ ከሆነ ንብረቱ ሊመለስ የሚችለው ታክስ ከፋዩ በፍርድ ቤት ስለሌሎች ዕዳዎች ወሳኔ አሰጥቶ ሲመጣ ብቻ ነው፡

# ክፍል 3

## <u>በምድብ "ለ" የሚገኙ የግብር ዘመናት የወዝፍ ዕዳ ቀሪ አደራረግ</u>

## 7. <u>የወዝፍ የታክስ ዕዳ ቀሪ አደራረግ ሥርዓት</u>

1/ በምድብ "ለ" ወስጥ ለሚገኝ የግብር ዘመን ታክስ ተወስኖ የታክስ ወሳኔ ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ በዚህ አንቀጽ በሌሎች ንዑስ አንቀጾች የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚፈለግበት ወዝፍ የታክስ ዕዳ ወለድ እና/ወይም መቀጫ ብቻ ከሆነ ዕዳው ቀሪ ተደርጓል፡፡

2/ የታክስ ዕዳ ምህረትን የሚመለከተው የማግስት ወሳኔ ከማስጠቱ በፊት የታክስ ኦዲት ተደርጎ የታክስ ወሳኔ ማስታወቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ በምድብ "ለ" ወስጥ ለሚገኝ የግብር ዘመን ዋና (ፍሬ) ታክስ፣ ወለድ ወይም መቀጫ ያለበት ከሆነ ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ወስጥ ማግስት የታክስ ዕዳን ለሚቃለል በሰጠው ወሳኔ ለማጠቀም የሚፈጠ መሆኑን ለታክስ ባለስልጣኑ ካሚለከተና፡-

ሀ) በክፍያ ጊዜ ስምምነት ማሰረት የሚከፍል ከሆነ የፍሬ ታክሱን 25 በመቶ በቅድሚያ በማካፈል ቀሪወን 75 በመቶ በአንድ ዓመት ወስጥ ለማከፈል የክፍያ ጊዜ ወል ተፈራርሞ በወሉ በተገለፀው ጊዜ ወስጥ ከፍሎ ካጠናቀቀ ወለድና መቀጫው ይነሳል፡፡ በማከፈያ ጊዜ ወስጥ ተጨማሪ ወለድ እና መቀጫ አይታሰብበትም፡፡

ለ) በ30 ቀናት ወስጥ ፍሬ ታክሱን ከከፈለ፡-

1. ከፍሬ ታክሱ ማጠን 10 በመቶ ተቀናሽ ይደረግለታል፡፡

2. የፍሬ ታክሱን 90 በመቶ ብቻ ይከፍላል፡፡

3. በታክስ ወሳኔው መሠረት የሚከፈለው ወለድና መቀጫ ቀሪ ይደረጋል፡፡

3/ በማግስት ወሳኔ ማሰረት ለማስተናገድ ያማለከተ ታክስ ከፋይ በደረሰው የታክስ ወሳኔ ማስታወቂያ ላይ በታክስ ወሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት፣ በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም በየደረጃው ባለ ፍርድ ቤት ያቀረበወን የታክስ ክርክር ያቋረጠ ስለመሆኑ ጠቅሶ ለታክስ ባለስልጣኑ ለዚህ ዓላማ በተዘጋጀው ቅጽ መሠረት ማመልከት አለበት፡፡ ሆኖም የመቀጫ ወለዱ ዕዳ መነሳቱን የሚገልጽ ማስረጃ ከታክስ ባለስልጣኑ ሊሰጥ የሚችለው ታክስ ከፋዩ ክርክሩን ያቋረጠ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ አግባብ ካለው አካል ሲያቀርብ ይሆናል፡፡

4/ ታክስ ከፋዩ በማግስት ወሳኔ ማሰረት ለማስተናገድ ካማለከተ የታክስ ባለሥልጣኑ በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም በየደረጃው ባለ መደበኛ ፍርድ ቤት የተሰጠወን ወሳኔ በመቃወም አቤቱታ ያቀረበበትን የታክስ ክርክር የተወ ስለመሆኑ ጉዳዩ ለተያዘበት አካል እና ለታክስ ከፋዩ በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተማለከተው ቢኖርም ታክስ ከፋዩ ለፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ በፍርድ ወሳኔ መሠረት የግብሩ ማጠን የተሻሻለ ከሆነና ይህ የተሻሻለው ማጠን ግብር ከፋዩ ካስያዘው ገንዘብ ያነሰ ከሆነ ልዩነቱ ለታክስ ከፋዩ ይማለሳል፡፡

6/ ማግስት የታክስ ዕዳን የሚቃለል ውሣኔ ከማስጠቱ በፊት የማከፈያ ጊዜ ስምምነት የገባና በማከፈል ላይ ያለ ታክስ ከፋይ በወሳኔው ማሰረት ለማስተናገድ ከተስማማ፡-

ሀ) ቀደም ሲል በምድብ "ለ" ወስጥ ለሚገኝ የግብር ዘመን የተከፈለ ወለድና ቅጣትን ሳይጨምር የተከፈለው ጠቅላላ ክፍያ ከፍሬ ታክሱ የበለጠ ከሆነ ባለበት ይጠናቀቃል፡፡

(ለ) ቀሪ የታክስ ዕዳ ካለው ቀደም ሲል የመክፈያ ጊዜ ስምምነት ላይ የነበረው ዉል ተሰርዞ ቀሪ ፍሬ ታክሱን 25 በመቶ በቅድሚያ በመክፈል ቀሪወን ታክስ በአንድ ዓመት ጊዜ ወስጥ ለመክፈል አዲስ የክፍያ ጊዜ ስምምነት ዉል ሚፈረም አለበት፡፡

7/ ገቢወን አስታወቆ የከፈለ ሆኖ የታክስ ወሳኔ ማስታወቂያ ያልደረሰው ታክስ ከፋይ በታክስ ኦዲት መሠረት የታክስ ወሳኔ ማስታወቂያ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ወስጥ በመቅረብ በታክስ ዕዳ ሚቃለያው የመንግስት ውሣኔ ማሰረት ማስተናገድ ከፈለገ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ሀ) እና (ለ) በተገለጸው መሠረት ማስተናገድ ይቻላል፡፡

8/ ገቢወን አስታወቆ ያልከፈለ ታክስ ከፋይ ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ወስጥ ቀርቦ ገቢወን ካስታወቀ፡ -

ሀ) የሚከፈል ታክስ ባይኖር የሚጠየቀው መቀጫ እና/ወይም ወለድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ቀሪ ይደረጋል፡፡

ለ) የሚከፈል ታክስ ካለ እና ፍሬ ታክሱን ሙሉ በሙሉ ከከፈለ ፍሬ ታክሱ ላይ የሚሰላው ወለድና መቀጫ ቀሪ ይደረጋል፡፡

ሐ) ታክስ ከፋዩ ያስታወቀወን ገቢ ትክክለኛነት ለሚረጋገጥ የታክስ ኦዲት ተደርጎ የታክስ ወሳኔ ማስታወቂያ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ 30 ቀናት ወስጥ በመቅረብ በመንግስት ውሣኔ ማሰረት ማስተናገድ ከፈለገ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ሀ) እና (ለ) በተገለጸው መሠረት ማስተናገድ ይችላል፡፡

9/ ታክስ ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ማሰረት የታክስ ዕዳን ለማቃለል በተሰጠው የመንግስት ወሳኔ ለመጠቀም የሚጠ ሚሆኑን ለታክስ ባለስልጣኑ ካላሣከተ በመንግስት የታክስ ዕዳ የሚቃለል ውሣኔ ማሰረት ማስተናገድ እንዳልፈለገ ተወስዶ መደበኛው የታክስ ሕግ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

10/ ታክስ ከፋዩ በመንግስት የታክስ ዕዳ የሚቃለል ውሣኔ ማሰረት በዚህ ምድብ ወስጥ ለሚገኝ የግብር ዘመን የታክስ ዕዳ የመክፈያ ጊዜ ስምምነት ገብቶ በስምምነቱ ማሰረት በአንድ ዓመት ወስጥ ክፍያወን አጠናቆ ካልከፈለ የታክስ ዕዳ የሚቃለል ውሣኔ ከማሰጠቱ በፊት የነበረና ያልተከፈለን ፍሬ ታክስ ወለድና ቅጣት በታክስ ሕጉ ማሰረት መክፈል የሚገባው ሲሆን ባልተከፈለው ታክስ ላይ መደበኛው የታክስ አስተዳደር ሕግ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

11/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ወሳኔ መሠረት ምህረት ከተደረገው የታክስ ዕዳ ማጠን በላይ ያለ የምድብ "ለ" የታክስ ዕዳ ለገንዘብ ሚኒስቴር እየቀረበ በምህረት ቀሪ ይደረጋል፡፡

## 8. <u>በዕዳ ምክንያት የተያዘ ሀብትና ንብረት</u>

1/ ታክስ ከፋዩ የታክስ ዕዳን ለማቃለል በተሰጠው የማንግስት ውሣኔ ማሰረት በምድብ "ለ" ወስጥ የሚገኝን የግብር ዘመን ፍሬ ታክስ በአንዴ ወይም በክፍያ ጊዜ ስምምነት ማሰረት ከፍሎ ከጨረሰ የታክስ ባለስልጣኑ በታክስ ዕዳ የተያዘ የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያለወን ዕግዱን በማንሳት ንብረቱን ለታክስ ከፋዩ ይመልሳል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ማሰረት የታክስ ዕዳወን ከፍሎ የጨረሰ ታክስ ከፋይ ክፍያወን ከፍሎ ካጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ወስጥ ንብረቱን ለሚከብ አመልክቶ የርክክብ ሂደቱን ካልጀመረ ንብረቱ እንደተተወ ቆጥሮ የማንግስት ሀብት ሆኖ ይማዘገባል፡፡

3/ ታክስ ከፋዩ በዚህ ምድብ ወስጥ ለሚገኝ የግብር ዘመን የታክስ ዕዳን ለማቃለል በተሰጠው የማንግስት ውሣኔ የፍሬ ታክሱን 25 በመቶ በቅድሚያ ከፍሎ እስከ አንድ ዓመት የመክፈያ ጊዜ ስምምነት የተፈራረመ ከሆነ የታክስ ባለስልጣኑ ለዕዳ ማካካሻ የያዘወን የማይንቀሳቀስ ወይም የሚንቀሳቀስ ንብረት ታክስ ከፋዩ እንዲሰራበት ለፈቅድ ይችላል፡፡ ታክስ ከፋዩ ዕዳወን ሙሉ በሙሉ ከፍሎ ሲያጠናቅቅ እግዱ ተነስቶ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ማሰረት የሚንቀሳቀስ ንብረትን ታክስ ከፋዩ እንዲሰራበት በታክስ ባለስልጣኑ የሚፈቀደው ባልተከፈለው ታክስ ማጠን (ወለድና ቅጣትን ጨምሮ) የባንክ ዋስትና ካስያዘ ነው፡፡

5/ በምድብ "ለ" ወስጥ በሚገኝ የግብር ዘመን ታክስ ተወስኖ መክፈል ባለበት ጊዜ ባለመክፈሉ ምክንያት ለታክስ ዕዳው ማካካሻ ይሆን ዘንድ የተያዘ የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ ሀብት ዕዳው ተከፍሎ ሳይጠናቀቅ ለባለሀብቱ ተመላሽ የሚደረገው የግብር ዕዳው የሚፈለግበት ድርጅት በኢኮኖሚው ወስጥ በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ሲሆን ብቻ ነው፡፡

6/ በኢኮኖሚው ወስጥ በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ድርጅት መሆኑን ለሚያጋግጥ የሚቀርበው ማስረጃ በሚኒስቴሩ ይወሰናል፡፡

# ክፍል 4

# <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

## 9. <u>የአፈጻጸም ስርዓት ስለማዘርጋት</u>

የገቢዎች ሚኒስቴር ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይችላል፡፡

## 10. ተፈጻሚነት የሌላቸው መመሪያዎች

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የገቢዎች ሚኒስቴር መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ለተሸፈኑ ውሳኔዎች አፈጻጸም ብቻ ጥቅም ላይ አይውሉም፡

1/ የታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ መመሪያ ቁጥር 137/2010 (ከነማሻሻያው)

2/ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ መመሪያ ቁጥር 142/2011

## 11. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሚያዝያ 28 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሚያዚያ 26 ቀን 2012 ዓ.ም

አህመድ ሽዴ
የገንዘብ ሚኒስትር